ሰፊው ሕዝብ ከትግሉ ሌላ አማራጭ የነፃነት መንገድ የለውም:: እንዴን የባርነት ቀን በር አውልቆ በሌላ መጠመድ አይፈለግም:: የግፍ ሰንሰለትን ለዘለዓለም ይሰባብራል:: በሰፊው ሕዝብ ስም ሲገዙና፣ በሰፊው ሕዝብ ስም ሲነዱ የሚሹ መሰሪና ወላዋይ ክፍሎች ሁሉ በአብዮት እግሩ ይረገጣሉ:: በንቅናቄ ክንዱ ይደቃሉ:: አሁን ከመንታ መንገድ ተደርሶአል:: መካከለኛ መንገድ የለም:: ባርነት ወይም ነፃነት:: ፋሽዝም ወይም ዲሞክራሲ:: የጥቂት መኰንኖችና የአድርባዮቻቸው ገዥነት ወይም የሰፊው ሕዝብ ሥልጣን:: ምርጫዎቹ እነዚህ ናቸው:: ሕዝቡ የፊተኞቹን አይመርጥም:: ለሁዋለኞቹ ይታገላል:: ታግሎም ያሸንፋል::

ፀረ—ሕዝብና ፀረ—ዴርጊት ኃይሎች ይደቀቁ!

የምርጥ መኰንኖች ሥልጣን ወደ ገደል!

ሰፊው ሕዝብ ይታገላል:: ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል!